ስልጣንና ህገ-መንግስት በኢትዮጵያ....

መንግስታት በየጊዜው በተለወጡ ቁጥር ህገ-መንግስትን በህግ አርቃቂ አካላት በሚርቀቅና በማሻሻል ለሚመሩትና ለሚያስተዳድሩት ማህበረሰብ ጠቃሚ ከለላና ጠባቂ ሆኖ ህገ-መንግስት የአንድ ሀገር የበላይ ህግ ሆኖ ይረቀቃል። የህግ አወጪውም ክፍል በህገ-መንግስቱ መሰረት ህግ ያወጣል።ስራ አስፈጻሚው ክፍልም በህግ መሰረት ይሰራል የሚለው የህገ-መንግስቱ ጽንሰ ሃሳብ የህገ-መንግስትን የበላይነት ያረጋግጣል።

ህገ-መንግስት በመሰረቱ በዜጎች መበት፣ዲሞክራሲ፣የነፃ እንቅስቃሴና ስልጣን የህዝብ አካል በሚሉ ሃሳቦች የተመረኮዘ ቢሆንም እንኳን ከንጉሰ ነገስታቱ የህገ-መንግስት ረቂቅ ጀምሮ ያሉት ህገ- መንግስታዊ ረቂቆች ባገሪቱ ያለውን የሃይል ሚዛን ባልተዛባ ሁኔታ የዜጎችን መበት የሚያረጋግጡ ረቂቆች ሆነው አያውቁም።

የኢህአዴግ ህገ-መንግስት ስልጣን ለተለያዩ አካላት የመከፋፈልና ስልጣንን ለህገ-መንግስቱ ተገዢ ላልሆኑ በፓርቲው ጀሌዎች ታጥሮ ያለና የዳኝነቱን ክፍል ነፃነት የሚረጋግጥ አይደለም፡በህግ ሰፍረው የሚጉ የህግ የበላይነትን የሚያረጋግጡ አንቀጾች በፓርቲው ፈላጭ ቆራጭ አመራሮች ያለ ምንም ገደብ በቀላሉ ሊጣሱና ሊረገጡ የሚቻሉ ናቸው፡የገዢው ፓርቲ አባሎች በህዝብ ላይ ለሚያደርሱት አፈና ግድያና የሰብሃዊ መበት ረገጣዎች የስልጣንን የበላይነት የሚቃወምም ሆነ የሚከላከል ብሎም የህገ-መንግስቱን መሰበር የሚያረጋግጥ ነጻ የሆነ የህግ አካል የለም።

ነፃ የሆነ የዳኝነት አካል መኖር የዲሞክራሲ አንዱ ገጽታ ነው።የኢህአዲግ ህገ-መንግስታዊ አንቀጽ 79/3 "ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በመሉ ነፃነት ያከናወናሉ።ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።"ይላል ግን በየጊዜው በየፍርድ ቤቶች ከገዢው ፓርቲ ያፈነገጠና የኢህአዴግ ኢሰብሃዊ የዜጎች አፈናና ጭፍጨፋ አሜን ብለው ሳይቀበሉ ተቃወሟቸውን ያሰሙንፁህ ዜጎች ገዝው ፓርቲ ባሴረላቸው የሃሰት ወንጀላና በሃሴትነት ባስቀመጣቸው ዳኞች ሐሴተኛ ወሳኔ ለእስራት፣ለግርፋት፣ ብሎም ለግድያ የተዳረጉትን ንፁህና ሰላማዊ ዜጎቻችን እሮሮ የየእለቱ ዜና ነው።የኢህአዴግ ህገ-መንግስታዊ ረቂቅ በህዝብ ሃሳብና ፍላጎት የተመረኮዘ ሳይሆን ጥቂት ለዚህ ህዝብ እኛ እናወቅልሃለን በሚሉ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣኖች በር ተዘግቶ ለጭቆናዊ አመራራቸው አመቺ በሆነ መልኩ የስልጣን ጥም እድሜ ማራዘሚያነት ያረቀቁት ነው።

በጥር 12 ቀን 2001 አ.ም በእነ አቶ ሚስ ዜናዊ እና በጀሌዎቻቸው አቅራቢነት ለይስሙላ ለህዝብ ተወካዩች ምክር ቤት ቀርቦ የፀደቀውና አወዛጋቢው የ27 ፌዴራል ዳኞች ሹመት ከተለያዩ ታላላቅ አገር በቀል ምሁራን ተቃውሞ የገጠመውና ከህገ-መንግስቱ አዋጅ ቁጥር 24/88 አንቀፅ 8''2 ጋር የሚጋጭ ነው።በዚህ አንቀፅ "ማንኛውም ሠው በመንግስት ህግ አወጪ ወይም አስፈፃሚ ወስጥ በአባልነት በሚያገለግልበት ጊዜ አጣምሮ የዳኝነት ሥራ ሊሰራ እንደሚይችል ይደነግጋል።" ነገር ግን በዚህ የዳኞች ፌዴራል ምርጫ በርካቶቹ በራሱ በ ኢህአዴግ ፓርቲ ወስጥ በአባልነት የሚያገለግሉ ናቸው።ምን ው ኢህአዴግ ራሱ ያረቀቀውን ህገ-መንግስታዊ ረቂቅ ዘንግቶት ነው ? ወይስ ሻሪም ፒሚም እኛው ነን ነው ? የዳኝነት አካላት ነፃና ከማንኛውም የፖለቲካ ወገን ገለልተኛ ካልሆኑ በዜጎች ላይ የህግ የበላይነትን ማስፈን ያዳግታል። ይህን የነ አቶ ሚስ ዜናዊን ሴራ የህግ የበላይነትን ሳይሆን የስልጣንና የጭቆናዊ ወታደራዊ አገዛዝን የበላይነት ፍንትው አድርጎ የሚያንፀባርቅ ነው።

ከጀሚል አብዱልቃድር
ጥር 26/2001 አ.ም